# ቃል የሚወጣውን ጭንቅላት አትንኩት

*ታህሳስ ፲፰ ቀን ሁለት ሺህ አንድ ዓ.ም.*

ለመልእክቴ መግቢያ አጭር ታሪክ እንዳነሳ ፍቅዱልኝ።

ከዚህ በፊት በአንድ ጽሑፍ የጠቀስኩት ቮልቴር የተባለ ፈላስፋ ከሶስት ክፍለ-ዘመናት በፊት የራሱን ህይወት ሰውቶ ኢፍትሐዊነትን በሚታገልበት ወቅት ቀጥቅጠው በሚገዙ ገዥዎች በተደጋጋሚ ይታሰርና ይደበደብ ነበር። አንድ ቀን ጌታው ባለበት ጮክ እያለ ሲናገር "ከየት የመጣ ውርጋጥ ነው እንዲህ እንዳሻው የሚጮህ" ብለው ጥላ ተሸካሚዎቻቸውን ሲጠይቁ አሁንም ቦልቴር ጮቅ ብሎ "ጌታየ እንደ እርሶ ትልቅ ስም የሌለው ነገር ግን ባለችው ስም መከበር እንጅ ውርጋጥ መባል የማይገባው ሰው" ብሎ ይመልሳል። ጌታውም በመልሱ ተናደው ከመቅጽበት "እስር ቤት ውሰዱና ቀጥቅጡት" ብለው ያዝዛሉ። የቮልቴርን ድንቅ ስራዎች ያውቅ የነበረው የፖሊሶች አዛዥ ግን ጌታው ከፊቱ ዘወር ሲሉለት ለፖሊሶቹ "ደብድቡት ዳሩ ግን አንድ ቀን ታምር ሊያፈልቅ የሚችለውን ጭንቅላቱን እንዳትነኩት" ብሎ ትእዛዝ አስተላለፈ። ታምር ሰሪው ጭንቅላትም ዳኑ በኋላም ቮልቴር ታምር ሰራና ይኸው እኛም ሳይቀር በደግ ስራው ስናነሳው እንኖራለን።

የአገራችንን ወቅታዊ ጉዳይ በጥሞና ለሚከታተል ሰው ፈልጎትም ባይሆን የወ/ሪት ብርቱካንን ታሪክ በአሁኑ ሰዓት በከፊልም ቢሆን ይረዳል ብዬ እገምታለሁ። የምሰጠው አስተያየት በፍትህና ሰብአዊ መብት መጓደል ላይ የተመሰረተ እንጅ ከራሷም ሆነ ከምትመራው የድርጅት አቋምና አላማ ጋር ፍጹም ግንኙነት የለውም። አዎ ሳልጠራም ቢሆን በአንድ አቢይ ጉዳይ ላይ ለመመስከር ነው። ለም-ጭንቅላት አላት! መድገም ካስፈለገ ልድገመው። አዎ ለም-ጭንቅላት አላት! በተጨማሪም ወደ ፊት ምን እንደሚመጣ መተንበይ ባልችልም እስካሁን ባየሁት ከብዙዎቻችን ጋ ቡጭቅጪቅ ብሎ የጠፋው ህሊና እርሷ ጋ እግዜር እንደሰራው ሳይሸራረፍ ቁጭ ብሎ የሚገኝ ይመስለኛል።

የቮልቴርን ጭንቅላት ስለ ለም- አእምሮ ጠቃሚነት የሚረዳ የፖሊስ አዛዥ አድኖታል። ታሪካችን እንደሚነግረው እኛ ግን ጥበበኛን፣ ጀግናን፣ ባለሙያንና ሌላም ሌላም ለመውጣት የሚጥረውን ሁሉ አባረን በለጋ እድሜው የማቀጨጭ እንዲያም ሲል የማጥፋት ባህሪ እናዘወትራለን። በዚሁ እንተወው እንጅ ከድሮ ጀምሮ የተፈጸሙትን በርካታ ግፎች መጥቀስ ይቻላል። በእውነቱ ከድህነታችን ቀጥሎ ይህ ሁሌ ያሳዝነኛል፤ ያሳፍረኛልም። ዛሬም በእኛ አገር የጠቃሚ-አእምሮን ወይም በህሊና-የመገዛትን ጠቃሚነት የሚረዱ ፖሊሶችም ሆነ ባለስልጣኖች መኖራቸው አጠራጣሪ ስለሆነ፤ ሰሚ ባገኝ በአጽእኖት የምጠይቀው ሲሆን ሲሆን አምላክ ካላችሁ ለአምላካችሁ፣ ከሌላችሁም ለለበሳችሁት ስጋ ስትሉ ወይዘሪት ብርቱካንን ተዋት፤ ከጨከናችሁ ደግሞ እጅና እግሯን እሰሩት ቃል የሚወጣውን ጭንቅላቷን ግን አትንኩት ብዬ ነው።

አመሰግናለሁ!

*በላይነህ አባተ* (abatebelai@yahoo.com)